ደረገ ። ሐጌ ዘካርያስ ኤርምያስ ሚልክያስን ጽ
ሩያን ምግባር ወሃይማኖት አደረገ ክብራቸው
ን መናገር ነው ። ዮሴዕ ዘሩባቤልን ጽሩያን
ምግባር ወሃይማኖት አደረገ ነሕምያ ከልዕ
ዕዝራ ጽሩያን ምግባር ወሃይማኖት ናቸው
እነዚህን ቢያወጡ ኢዮስያስ መርዶክዮስ ማ
ደሪያዎች ትሩፋን ም ዕፅድዋን ምግባር ወሃ
ይማኖት ናቸውና የሕገ እግዚአብሔር ማደ
ሪያ የሚሆን ያንዱም ያንዱም ሰው ልቡና በ
ምግባር በሃይማኖት የጸና ነው ። ያንዱም ያን
ዱም ሰው ልቡና በኢታምልክ የጸና ነው
አንድም ። የሰሎሞን እግዚአብሔር ማደሪያ
ው እመቤታችን እንደሆ ናት ከኃያላነ እስ
ራኤል የተመረጡ ከኃያላነ እስራኤል የተወ
ለዱ ስሳ ኃያላነ አእምሮ የሚሆኑ አስራሁለቱ
ሐዋርያት በዙሪያዋ አሉ ሁለቱን ዓሥር ሁለ
ቱን አሥር ብሎ ቊጥሮ ስሳ አላቸው ሁሉ
ም ሥልጣን የያዙ ናቸው ። ሰልፍ መንፈሳዊ
ንም የተማሩ ናቸው ። አንዱም አንዱም ሥል
ጣን ገንዘቡ ነው ። በሌሊት አደጋ ይመሰላሉ
የሌሊት አደጋ እንዲያስደነግፅ የሚያስደነግፁ
ናቸው ሐተታ እንዳለፈው ። ከአብርሃም ልጆች
ለይቶ እመቤታችንን ማደሯው አደረገ ። አራ
ቱ ወንጌላውያንንም ጽሩያን ምግባር ወሃይማኖ
ት አደረገ ። አራቱም ወንጌላት ፅሩያን ሕገጋ
ት ናቸው ወንጌላቱስ ወንጌላውያን ከለው ይ
ገባል ብሎ ክብራቸውን መናገር ነው ። ቊጥ
ር ሳይሹ አራቱን ሊቃነ ጳጳሳት ጽሩያን ምግ
ባር ወሃይማኖት አደረገ ። ክብራቸውን መንገ
ር ነው ። አንድም ተራ ይሰጧል አዕማዲሁ ገ
ብረ ዘብሩር አራቱ ወንጌላውያን ። ሰርዲኖስ
ዘምስለ ተርሴስ ኢዮጳሎግዮስ ዘምስለ ሰፎር
አራቱ ወንጌላት ምስማኩ ዘወርቅ አቊላፊሁ
ወአቊፋሊሁ ኢያሴሜር አራቱ ሊቃነ ጳጳሳት
ማደሯዎቹ ምዕመናንም ጽዕድዋን ምግባር ወ
ሃይማኖት ናቸው ። የሕገ እግዚአብሔር ማደሯ
የሚሆን ያንዱም ያንዱም ሰው ልቡና በምግ
ባር በሃይማኖት የጸና ነው ። የመቤታችንም ል
ቡናዋ ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ በማለት የጸና
ነው ።
አፈቅሮ ፈድፋደ እምአዋልደ ኢየሩሳሌም ።
ከኢየሩሳሌም ልጆች ይልቅ እንዲህ ያለ
ሰሎሞንን እወደዋለሁ ።
፲፩ ፃዓ ትርአያ አዋልደ ጽዮን ለንጉሥ ሰሎ
ሞን በአክሊል ዘአስተቀጸለቶ እሙ ።
ለንጉሥ ሰሎሞን ካለ ትርአያሁ ፤ ትርአያም
ካለ ንጉሠ ሰሎሞንሃ ቢል በቀና ነበር ፤ እ
ናቱ ቤርሳቤሕ ከንጉሥ ዳዊት ተካሳ ያቀ
ዳጀችውን ዘውድ ደፍቶ ንጉሥ ሰሎሞንን
ታዩ ዘንድ የጽዮን ልጆች ኑ ውጡ ። አ
ንድም አዝማደ እሙ ይላል የናቱ ዘመ
ዶች ኬልቲ ፌልቲ ያቀዳጁትን ዘውድ ደ
ፍቶ ንጉሥ ሰሎሞንን ታዩ ውጡ ።
እመ ዕለተ ሕማሙ ።
አዮንያስ መከራ አመጣበታለሁ ባለበት ቀን
ወእመ ዕለተ ስቅለቱ ።
እሰቅለዋለሁም ባለበት ቀን ።
ወእመ ዕለተ ሞቱ ።
እገለዋለሁም ባለበት ቀን ።
ወእመ ዕለተ መርዓሁ ።
በነገሠበት ቀን ።
ወእመ ዕለተ ፍሥሐ ልቡ ።
ነግሦ ልቡናውን ደስ ባለው ቀን እናቱ ከ
ንጉሥ ዳዊት ተካሳ ያቀዳጀችውን ዘውድ
ደፍቶ ንጉሥ ሰሎሞንን ታዩ ዘንድ ኑ ውጡ
አንድም ከኢየሩሳሌም ልጆች ይልቅ እን
ዲህ ያለ ሕዝቅያስን ፈጽሜ እወደዋለሁ
እናቱ ሕግ ያቀዳጀችውን ዘውድ ደፍቶ
አንድም አዝማደ እሙ ይላል የናቱ የሕ
ግ ዘመዶች ነቢያት ካህናት ያቀዳጁትን ዘ
ውድ ደፍቶ ንጉሥ ሕዝቅያስን ታዩ ዘንድ
የጽዮን ልጆች ውጡ ። ሰናክሬም ሲሸሽ ዘ
ውዱን ጥሎት ሄደ ነቢያት ካህናት አግኝ
ተው ላንተ ይገባሃል ብለው ደፍተውለታ
ልና ። ሰናክሬም መከራ አመጣበታለሁ ባለ
በት ቀን ። እሰቅለዋለሁም ባለበት ቀን ። እ

ከፋርስ ከባቢሎን ትወጫለሽ የሚል ቃልህን
አሰማኝ ይግ መጽሐፍ ከሆነ በጀመረበት ይ
ጨርሳልና ይኸም በጀመረበት ጨረሰ ።
፲፬ ጕይ አንተ ወልድ እኁየ ከመ ወይጠል።
ልጅ ወንድሜ እግዚአብሔር እንደ ፈቆ ።
ወከመ ወሬዛ ኀየል ውስተ አድባረ ድኁኃን
በአብርሃም በይስሐቅ በያዕቆብ አገር እንደ
ተሰማራ የዋልያ ወይፈን ። እንድም ውስተ
አድባር ድኁኃን ይላል ጽኑዓን በሚሆኑ ተራ
ሮች እንደ ተሰማራ የዋልያ ወይፈን እኔን
ለመራዳት ስትመጣ መር በል ያ ፈጣን ነው
ፈጥነህ አውጣኝ ።

ተፈጸመ መኃልየ ሰሎሞን ወስብሐት ለእግ
ዚአብሔር አሜን።

አነቃቅቶ ላስጀመረን አተጋግቶ ላስፈጸመን
እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባውና የዳ
ዊት ልጅ የሰሎሞን ምስጋና መላ ተፈጸመ
በውነት እንበለ ሐሰት ።